ታህሳስ 24 2004

# የጋራ ትግል፤ የጋራ አገር!

በጄኔራል ከማል ገልቹ የሚመራው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ጥላ ሥር ከሌሎች የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር ተባብሮ ለመታገል መወሰኑን ገሃድ አድርጓል። በዚህ ውሳኔ ሳቢያም በኢትዮጵያ የሰፈነውን ዘረኛ አምባገነን ሥርዓት አስወግደን በምትኩ የግልና የወል መብቶች የተከበሩባት፤ ፍትህና እኩልነት የሰፈኑባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመፍጠር በምናደርገው ትግል ውስጥ ኦነግ አዎንታዊ የሆነ ወሳኝ ሚና እንዲኖረው የሚያደርግ አዲስ ሁኔታ ተፈጥሯል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ኦነግ በወሰደው አቋም የተሰማውን ደስታ ይገልፃል። "በጋራ ትግል የጋራ ጠላታችንን አስወግደን፤ የጋራ አገራችንን ተባብረን እንገነባለን" የሚል ብሩህ ተስፋ ፈንጥቆልናል።

ግንቦት 7፣ ይህንን ለሁላችንም እጅግ አስፈላጊና ፋና ወጊ የሆነውን ውሳኔ የመስጠት አርቆ አሳቢነት እና ድፍረት ላገኙት የኦነግ የአመራር አካላት ያለውን አድናቆት ይገልፃል።

ግንቦት 7 ይህን አድናቆቱን እየገለፀም የኦሮሞ ነፃነት ግንባር በአንድ ጠንካራ አመራር ሥር ሆኖ የኦሮሞን ህዝብ ጥቅምና መብት ብቻ ሳይሆን የሃገሪቱን ዜጎችና ሕዝቦች በሙሉ መብቶችና ጥቅሞች በጋራ ለማስከበር በሚደረገው ትግል ተሳታፊ ቢሆን ኖሮ ሊገኝ የሚችለውን ሕዝባዊና ሃገራዊ ጥቅም ግዙፍ እንደሚሆን አይስተውም። በዚህም ምክንያት ነው የኦሮሞ ምሁራን በተለይ የፖለቲካ ልሂቃኑና ኦነግ በአንድነትና በአንድ ድምጽ እየተናገሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለነፃነት፣ ለፍትህና ለዲሞክራሲ በሚያደርገው የጋራ ትግል የኦሮሞን ሕዝብ ታላቅነት የሚመጥን ሃገራዊ የኃላፊነት ሚና እንዲጫወቱ ግንቦት 7 እና በርካታ ወገኖች ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ የቆዩት። የተደረገው ጥረት ለጊዜው ባይሳካም በአጭር ጊዜ እንዲሳካ የተቻለውን ሁሉ መደረግ አለበት ብሎ ግንቦት 7 ያምናል።

ስለሆነም ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ከሌሎች የኦነግ አካላት፤ ሌሎች የኦሮሞ ታጋዮች እና በአገራችን ከሚቀንሳቀሱ የነፃነትና የዲሞክራሲ ኃይሎች ሁሉ ጋር የሚያደርገው ግልጽና ቅን ውይይት ይቀጥላል። ጥረቶቻችን ፍሬ አፍረተው አሁን ከደረስንበት የሰፋ መቀራረብ እንፈጥራለን ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

ግንቦት 7 ከዚህ በላይ ያስቀመጠውን የተባብሮ መሥራት እምነቱን እንደያዘ የዲሞክራሲ ኃይሎች በተፈጠረው አዲስ ሁኔታ ተበረታተን የኅብረት አድማሳችንን የምናሰፋበት መንገዶችን መቀየስና ተግባራዊ እንቅስቃሴዎቻችንን አጠናክረን መቀጠል ይኖርብናል የሚል የጸና አቋም አለው።

በኢትዮጵያ ውስጥ የምንገኝ ዜጎችም ሆን ቡድኖች ሁሉ የወደፊት እጣ ፈንታችን የተሳሰረ መሆኑን አውቀን፤ በጋራ ከሠራን በዴሞክራሲያዊ አንድነት ላይ የጸና መሰረተ ላይ የቆመችና ለሁላችንም የምትመች አገር መፍጠር የምንችል መሆኑን ተገንዝበን እና በጄኔራል ከማል ገልቹ በሚመራው ኦነግ አዲስ አቋም

ተበረታተን የኅብረት አድማሳችንን ለማስፋት በርትተን እንሥራ። ለጋራ ህልውናችን እና ለወደፊቱ ብሩህ ተስፋችን ስንል በሆደ ሰፊነትና አርቆ አስተዋይነት ጊዜዓዊ አለመግባባቶችን እንድናስወግድ ግንቦት 7 ጥሪ ያደርጋል።

በኅብረት ትግል ከመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ነፃ እንወጣለን!

በጋራ ትግል የጋራ አገራችንን እንገነባለን!!!